# መለስ ይታወሳል፤ ገብረማርያምም ይዘከራል!

ዮናስ 08/29/13

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ አንድ ሠው ሁለት ስሞች አሉት፤ የመዝገብ ስም እና የመጽሐፍ ስም፤ ወይም ስጋዊና መንፈሳዊ ስም ፡፡ በርግጥ መንፈሣዊ ስማቸውን ለሥጋዊ ስማቸው በተመሣሣይ የሚጠቀሙበት መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ የመዝገብ ወይም ስጋዊ ስማቸውን በማሣጠርና ቅጥያዎች በመጨመር አልያም ደግሞ በተለየ ከሁኔታዎች ጋር ተያይዞ በሚመጡ መደበኛ ያልሆኑና በግለሠቦቹ ቤተሠቦች እና ጓዶች አካባቢ በመጠሪያነት የሚያገለግሉ ስሞች ያሏቸው ግለሠቦች መኖራቸውም እርግጥ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ግን ከላይ እንደተጠቀሠው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በመዝገብ ወይም በሥጋዊ ስማቸው በምድራዊ ህይወታቸው ይገለገላሉ፡፡ የመታወቂያቸው የትምህርትቤታቸው ወይም ደግሞ የሥራ ቦታቸውና ባጠቃላይ በማህበረ ኢኮኖሚ ፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ግልጋሎት ላይ የሚውለው ባለቤት ስጋዊ ስማቸው ወይም የመዝገብ ስማቸው ነው፡፡

በሰማያዊ ህይወታቸው መጠሪያቸው ደግሞ የመጽሃፍ ስማቸው ነው፡፡ አበበ በምድር ወልደገብርኤል በሠማይ እንደማለት፡፡ አበበ በምድር ላይ በሚያደርጋቸው የሥጋ ጥሪዎቹ ሁሉ መለያና መታወቂያው ነው፡፡ ወልደ ገብርኤል ደግሞ በመንፈሣዊ ህይወቱ መለያና መታወቂያው ይሆናል ማለት ነው፤፤

አበበን በሠራው ምድራዊ ታሪክ ሁሉ አበበ የተወለደበት ማህበረሠብ ቢያውቀውም ወልደገብርኤልነቱን የሚያውቁት ግን ጥቂቶች ቤተሠቦች እና ንስሃ አባቱ (መንፈሳዊ አባቱ)(ካህኑ) ብቻ ናቸው፡፡

አበበ የህይወት ዘመኑን ሲጨርስ በሠራው ታሪክ ልክ በአበበነቱ ይወደሣል፤ ይነቀፋል ከሁለት በአንዱ ሲታወስ ይኖራል፡፡ አበበ በመንፈሣዊ ህይወቱ ባደረገው ልክ ወልደገብርኤል በምድር ይዘከራል፡፡ በሠማይም ይጠየቃል እንደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት አስተምህሮ፡፡

በምድር በሥራው ልክ ሲታወስ ወይም ሲነቀፍ የሚኖረው አበበ በመንፈሣዊ ህይወቱ በሠራው ልክ እንደወልደገብርኤል ሆኖ በቀኝ ወይም በግራ ይቆማል ማለት ነው፡፡ ሠው በሥራው ይመዘናል እንዲባል አበበ በምድር ለሠማዩ ወልደገብርኤል ወሣኝ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የዛሬ አንድ ዓመት የሞቱት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስን እንደጠቅላይ ሚኒስትርነታቸውና እንደመሪነታቸው በሥጋዊ ስማቸውና ተግባራቸው እናውቃቸዋለን፤ ስናውቃቸው ደግሞ አቶ መለሥ ዜናዊ አስረስ በሚለው የመዝገብ ስማቸው ነው፡፡ ማንኛውም ዜጋ የመሠለውን እምነት የመከተልና የማራመድ ህገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡ ምንም እንኳን አቶ መለስ የየትኛው እምነት ተከታይ መሆናቸውን ለአስተዳደሩ ሲሉና የብዙ ሃይማኖቶች ባለቤት በሆነችው አገር ላይ መግለጽ ተገቢ አለመሆኑን በመረዳት በህይወት በነበሩ ጊዜ ባይነግሩንም፤ የየትኛው ሃይማኖት ተከታይ መሆናቸውን ግን ብዙዎቻችን መገመታችንና ከእረፍታቸውም በኋላ ገብረማርያምነታቸው ሲገለጽ ግምታችን ትክክል መሆኑን ማረጋገጣችን እሙን ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሠው መሠረት አበበ እንደ አበበ በምድራዊ ህይወቱ እንደሚታወቀውና ሃገራዊ እና ምድራዊ ግልጋሎት እንደሚያገኘው ሁሉ በመንፈሣዊ ግልጋሎትም እንደወልደገብርኤል ማግኘቱ ቅርጽና ይዘቱ ይለያይ እንደሆነ እንጂ በየትኛውም ሃይማኖት ሠዎች ምድራዊ ህይወታቸውን በጨረሡ ጊዜ በፀሎት መታወሣቸውና መዘከራቸው ያለ ነው፡፡

አቶ መለስ እንደ አቶ መለስ በሠሩት ምድራዊ ስራቸው ታሪክ ነውና መታወሣቸው በክፉም ሆነ በበጎ አይቀሬ መሆኑን በመርህ ደረጃ ከተሥማማን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንደመሆናቸው ደግሞ እንደገብረማርያም በምድር ሳሉ ከመንፈሣዊ አባቶቻቸው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነትና እሣቸው በሚያውቁት (ሠማያዊና መንፈሣዊ ጉዳይ የግልና ሚስጥር እንደመሆኑ) እንዳገለገሉት እንደፆሙትና እንደፀለዩት ሁሉ ነፍሣቸው ባረፈችም ሰዓት በመንፈሣዊ አገልግሎት መዘከራቸው የሥርዓት ቤተክርስቲያኒቱ ህግጋት ነው፡፡

ይህን ጉዳይ ያነሣሁበት ምክንያት ግልጽ ሳይሆን የቀረ ዓይመስለኝም፡፡ በተለይም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ በሥጋ ከተሠናበቱን አንድ ዓመት የሞላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መለስ እንደ ግለሰብ እና እንደ ሃገር መሪ እንዲሁም እንደ ፓርቲያቸው አቶ መለስና ጓድ መለስ በተለያዩ ፕሮግራሞች በምድር እየተወሡ መሆኑ የነገሬን ዋነኛ ምክንያት የሚገልጽ ይመስለኛል፡፡

ዋናው ጉዳዬ ግን ከዚህ የአቶ መለሥ ትውስታና ዝክር ጋር ተያይዞ ከዜሮ ድምሩ ፖለቲካ መንደር በምንም መንገድ ይሁን በምን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ምድራዊ ትውስታና ሠማያዊ ዝክር በመለሥና በገብረማርያም የተጀመረ ይመሥል የማብጠልጠልና የማጠልሸት ዘመቻ የመጀመሩ ሚስጥር ማመላከት ነው፡፡

አቶ መለስ እንደመለስ በሙት ዓመታቸው ነሐሴ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የታወሡት በጉለሌ የመለስ የእጽዋት ማዕከል "የመለስ ዜናዊን የህዝብ መናፈሻና ቤተመፃህፍት" የመሠረት ድንጋይ

በማስቀመጥ ሲሆን በአዲስ አበባና በተለያዩ ክልሎችም በሥማቸው የመታሠቢያ ፓርኮችን በመሠየምና በችግኝ ተከላ ሥነ ሥርአቶች መለስ ታውሠዋል፡፡ በተለይ በጉለሌው የእጽዋት ማእከል ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሣለኝን ጨምሮ ከፍኛ የመንግስት ባለሥልጣናትና፣ የአፍሪካ መሪዎችና ተወካዮች፣ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆኑ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላትና ባለቤታቸው ወ/ሮ አዜብ መስፍን በተገኙበት የተከበረና ደማቅ የነበረ የትውስታ ሥነሥርዓት ነው፡፡

በዚሁ የመታሠቢያ ሥነ ሥርዓት የአቶ መለሥ የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸው የተወሱ ሲሆን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ደግሞ አቶ መለስ እንደገብረ ማርያም በጸሎት ሥነ-ሥርዓት ተዘክረዋል፡፡

በጉለሌው የእጽዋት ማዕከል ላይ የተገኙት የአቶ መለስ ባለቤት ካደረጉት ንግግር "የአዲሲቱ ኢትዮጵያ አናፂና መሪ የነበሩት አቶ መለስ አንደኛ ዓመት እንደዛሬ ዓመቱ በለቅሶ የሚዘከር ሣይሆን ራዕያቸውን ለማስፈፀም በእልህ በመግባት ነው" የምትለው ሃራግ ለትርክቱ ጥሩ ማሣያና አስረጅ ሆና አግኝቻታለሁ፡፡

ስለሆነም በከሠሩት ፖለቲከኞቹ መንደር ስለመለስ መታሠቢያ ምን እየተባለ ነው? የመለሥ ራዕይ የመታሠቢያ ዝግጅት ከከሠሩት ፖለቲከኞቹ ትርክት አንፃር እንዴት ይመዘናል? የሚሉትንና መለስን እንደገብረማርያም ይህ ጽሁፍ ይተርካልም፤ ይዘከራልም፡፡

የዜሮ ድምር ፖለቲካው ስብስቦች ሴራና ሃሣብ የሚንፀባረቀው በዜሮ ድምር ቅጥረኛ በሆኑና በነፃ ፕሬስ ስም በተቋቋሙ ጋዜጦች ስለመሆኑ በገዢ ሥርዓቱ በኩል በተደጋጋሚ መገለጹ ይታወሣል፡፡

ከብዙ ንባብና ምዘና በኋላም ይህ የገዢው ፓርቲ ገለፃ ፍረጃ ሳይሆን ትክክለኛና ሥነ ፖለቲካዊ ጥናትን መሠረት ያደረገ እንደሆነ መገንዘብ በመቻሌ ለዚህ ትርክት አስረጅ የሚሆኑ ነጥቦችን የወሰድኩት ስብስቡን ከሚወክሉ ሁለት ሃገርኛ ጋዜጦች ላይ ነው ፡፡

የመጀመሪያዋ የኛ ፕሬስ የተሠኘችው ጋዜጣ ስትሆን በሁለት ቦታዎች ላይ ለጽሁፌ መነሻ የሆነኝን ሃሣብ አሥፍራለች፡፡ "ህዝብ ኢህአዴግ የፈጠረውን "አምላክ" የማምለክ ግዴ የለበትም" የሚል ርዕሥ ከሠጠችው ርዕሠ አንቀጿ ለዚህ ጽሁፍ ተስማሚ የሆነው ፍሬ ነገር "መለስ ዜናዊ ብዙ ግድፈቶች የነበሩባቸው ስለመሆኑ ተሳስቶም ቢሆን ተናግሮ የማያውቀው ኢህአዴግ፣ ለአቶ መለስ ከሠጣቸው የቅድሥና ደረጃም አልፎ የአምልኮ መንፈስ በመላው አገሪቱ እንዲነግስ የማድረግ ፕሮፖጋንዳውን አጠናክሮ ገፍቶበታል፡፡ እንዲያውም አሁን ስጋት እየሆነ የመጣው ወደፊት ይታነፃል ተብሎ የሚጠበቀውን "የመለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን" ወደመለስ ዜናዊ ቤተመቅደሥነት

ተለውጧል የሚባልበት ቀን እንዳይመጣ ነው” የሚለው ሲሆን ሁለተኛው የመከራከሪያ ጭብጥ የሠፈረው ደግሞ በዚህችው ጋዜጣ ላይ ነፃ ሃሣብ ዓምድ ባርኮት ዮሐንስ የተባሉ ፀሃፊ ያሰፈሩት ሃሣብ ነው፡፡ ሙሉ ትርክቱን እንድታነቡ እየጋበዝኩ ለዚህ ትርክት የመሟገቻ ነጥብ ግን ባርኮት ዮሐንስ ለጽሁፋቸው የሠጡት ርዕሥ ብቻ ነው ፡፡

“የመለስ ራዕይ” ቀርቶ፣ የፈጣሪ ቃል እንኳን የሚሠበከው በገደብ ነው፡፡ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ችግሮች የምንሠደደው እንዦ ደግሞ በ”መለስ ራዕይም” እንሠደድ እንዴ?....” ይላል ርዕሡ፡፡

ሌላኛዋንና ለሙግቴ ተስማሚ የሆነችውን የዜሮ ድምር ስብስብ ከ ለ”መለስ ራዕይ” የተዛባ ፍሬ ሃሣብ ያገኘሁት ደግሞ ከሌላዋና የዜሮ ድምሩ ስብስብ ወኪል ከሆነችው ኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ነው፡፡

ፀሃፊው መሃመድ ሃሠን ይባላሉ፡፡ “የአሚር ልደትና የመለስ ሙት ዓመት” የሚል ርዕስ ለተልፈሠፈሠው ትርክታቸው ሰጥተውታል፡፡ በዚህ ርዕሥ ሥር ካሠፈሯቸው ነጥቦች መካከልም ለዚህ ጽሁፍ የመከራከሪያ ጭብጥ ተስማሚ ሆኖ ያገኘሁት የሚከተለውን ነው፡፡

“ዛሬ ግን እየተከበረ ያለው ብቻ ሳይሆን ሁላችንም በግድ እንድናከብረው እየተገደድን ያለነው “የሃገሪቱን” ሙት ዓመት ነው፡፡ ያውም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተመረጠ ከሚሉን አንድ መሪ ጋር አብራ “የተቀበረች” ሃገር ሙት ዓመት”….

“አባቶቻችን የተነፈጉትን ዕድል እኛ ልጆቻቸው ካልሆነም ደግሞ የኛ ልጆች እነ አሚር (በእርግጥ እዛ ድረስ አይርቅም) ማግኘታችን ስለማይቀር፣ እውነታው በታሪክ ላይ ስለመሥፈሩ ቅንጣት ታህል ልንጠራጠር አይገባም፡፡ ያኔ በፈጠራ የሽብር ክስ ንፁሃን ዜጎችን፣ ጋዜጦችን፣ ፖለቲከኞችን፣ የሃይማኖት አባቶችንና ምሁራንን ከሃገር ስላባረሩት፣ ሃገሪቱን ወደብ አልባ ስላደረጓት፣ በዘርና በሃይማኖት ስለከፋፈሉን፣ ዴሞክራሲን አንቀው ስለገደሉት፣ ነፃውን ፕሬስ ስላሽመደመዱት፣ ሙስናን ስላንሠራፉት፣ የፈጠራን ክስ ስላስፋፉት፣ ፓርቲ የሃገርን ኢኮኖሚ ጠቅልሎ እንዲቆጣጠር ስላደረጉት፣ ደካሞችን ብቻ ሠብስበው መሪ ስላሣጡን፣ ህዝቡን ካድሬ በሚባል የደካሞች ስብስብ መተንፈሻ ስላሣጡት፣ ኢትዮጵያዊነትን ስለገደሉት አቶ መለስና ሥርዓታቸው ሁሉም ነገር ይፋ ይወጣል”…

እነዚህ እንግዲህ የመለሥ መታሠቢያን ተከትሎ መለስ ማነው በሚል መታሠቢውን ለማደክረትና ቁም ነገር አልባ እንደሆነ ለመግለጽ ከዜሮ ድምሩ ስብስብ አካባቢ የሚወረወሩ ድንጋዮችን የሚወክሉልኝና ለተነሣሁበት ሙግትም ጥሩ ማሳያ ሆነው ያገኘኋቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ስለመለስ ሙት ዓመት የመታሠቢያና የዝክር ስነ-ሥርዓትና ይገባቸዋል ወይም አይገባቸውም ወደሚለው ጉዳይ ከማምራቴ በፊት ከላይ የዜሮ ድምሩን ስብስብ ይወክላሉ የተባሉት ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የመለስን ራዕይና ኢትዮጵያዊ አንድመታ በአጭሩ መመልከት ተገቢና ፍትሃዊ ይመስለኛል፡፡

የዜሮ ድምሩ ስብስብ በስፋትና በጥልቀት የተልፈሠፈሠ ቅኔውን የሚቃኘው ለሜራው ያመቸው ዘንድ  የመለስን ራዕይ ከወጣቶች ጋር በማገናኘት ነው፡፡ መለስ ሥራ ያሳጣውን ወጣት ሃዘን እንዲቀመጥ  ኢህአዴግ እያስገደደው ነው፤ የሚል መዝሙር በተደጋጋሚ ብንሠማምና ከላይም ከዜሮው ድምር ወኪሎች ላይ ወስጄ ባሠፈርኩት ነጥብ የተመለከተ ቢሆንም፡- መለስ ለወጣቶች የእሱ ትውልድ ባለፈበት የጦርነትና የሠቆቃ ህይወት እንዳያልፉና የተሻለም ቀን እንዲመጣላቸው የሚመኝ መሪ ነበር፡፡ "ትግሉን የመጀረ አይጨርሠውም፣ የእኛ ትግል የዱላ ቅብብል እንጂ የማራቶን ሩጫ አይደለም፡፡ ስለዚህም ወጣቶች ተኪዎቻችን ናቸውና እናስተምራቸው፣ እናብቃቸው" የሚለውን ጽኑ አቋም በተግባርና በተጨባጭ ያረጋገጠ መሪ በመሆኑና፣ ለመቅደም፣ ለመታወቅና ለመወደድ የማይሻ ሠው በመሆኑ ህይወቱ ባለፈበት ሠዓት እንደአብነት የሚያዩት ወጣቶች የሃዘን እሮሮ ቢያሰሙና በእለተ ሙት ዓመቱ ባለቤቱ እንደተናገሩት በሥራ አስበውት ቢውሉ የአቋራጭ ስልጣን የሚሹትና ለዚሁም መሻታቸው ወጣቱን ተስፋ ያደረጉት ስብስቦች ቢትከነከኑ አይገርመንም፡፡

በትጥቅ ትግሉ ወቅት የህወሃት የትግል አጋር የነበረው ኢህዴን (ብአዴን) ጥንካሬ ይጎናፀፍ ዘንድ ህውሃት በሁሉም መስኮች ለራሡ የሚሠጠውን ያህል ትኩረት ለብአዴንም መስጠት እንዳለበትና ሊደግፈው እንደሚገባ ግልጽና ወደ ተጨባጭ ተግባር የተሸጋገረ ጽኑ አቋም ያራመደ መሆኑና በተጨማሪም ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ህወሃት በትጋት መንቀሣቀሥና ማገዝ እንደሚኖርበት አበክሮ ለማስጨበጥ በመሥራቱ ይህም ወደኋላ በተግባር መፈፀሙ የህወሃት የብአዴን፣ ደኢህዴን እና የኦህዴድ አመራሮችና አባላቱ ስለመለስ ራዕና የለውጥ ጠንሣሽነቱ ትዝታ ቢያነቡ እና ሙት ዓመቱንም በሥራ አሥበው ቢውሉ ያብከነከናቸው ስብስቦች ቢቆዝሙና ተሥፋ ቢቆርጡ  የሚጠበቅ ነውና አይገርመንም፡፡

የመለሥ ባለራዕይነት፣ የለውጥ ጠንሳሽና አንቀሣቃሽነት የታየበት ሌላው ታላቅ አብነት በ80 እና በ81 የተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ይህ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ወደቀጣዩ የትግል መድረክ ለመሸጋገር የሚያኮበኩብበት ወቅት ነበር፡፡ የአብዮቱ ቁልፍ ጥያቄዎች ዝርዝር ምላሽ ይጠይቁም ነበር፡፡ እናም መለሥ የዴሞክራሲና የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮትና የመንግስት ስልጣንና የኢትዮጵያ አብዮት፣ የመሬት ጥያቄና የኢትዮጵያ አብዮት በሚሉና የኤርትራ ህዝብ የነፃነት ንቅናቄን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እጅግ ጥልቅ ትንታኔ የሠጠባቸውን የመወያያ

መፃህፍት አዘጋጅቶ፣ የትግሉ ጎዳና በጠሩ መስመሮች ዙሪያ ግልጥልጥ ብሎ መታየት የሚችልባቸውን ንድፈ ሃሳባዊና ተግባራዊ ሃሳቦች በመቀመሩ፤ ኢህአዴግ የሚመሠረትበትን የማዕዘን ድንጋይ በማነጠፍ ይህን ራዕይና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ጥያቄ መፍትሄ የሠጠውን መለስ የትግል አጋሮቹ ቢያስቀጥሉና ሰውየውንም በሥራ አስበውት ቢውሉ ተገቢና ትክክልም እንጂ "ፕሮፖጋንዳ ነው" ቢባል ከስብስቡ የሚጠበቅ በመሆኑ አሁንም አይገርመንም፡፡

የመለስ ባለራዕይነትና የለውጥ ፈላጊነት የሚያመላክተው ሌላው ትልቁ አብነት ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ አስርት ዓመታት የበለፀጉ ሃገሮችን ጎራ እንድትቀላቀል ያስቀመጠው ራዕይ ነው፡፡ ይህ ራዕይ ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት ሁኔታ በተሟላ ደረጃ የምትላቀቅበትና የዳበረ ኢኮኖሚና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባለቤት የምትሆንበት ራዕይ መሆኑን እንኳንስ እኛ ዓለም አቀፉ ማህበረሠብ የመሠከረው ሃቅ ነው፡፡ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱም የዚሁ ራዕይ አካል ነው፡፡ ይህ እቅድ የኢትዮጵያን ማህበረ-ኢኮኖሚ መዋቅር ወደ ኢንዱስትሪ መርነት እንዲሸጋገር የሚያስችለውን ሁኔታ የሚፈጥር እንደሆን አሁን በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ እድል ተጠቃሚ የሆኑና የለውጡ አካል የሆኑ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውን ይህንኑ ሃገር የሚገነባ የመለስ ራዕይ ለማስቀጠል ቢምሉና ቢገዘቱ፣ ስለመለስም ያለጊዜው ማለፍ ማንባታቸው የግዴታ ሳይሆን ከባለ ብሩህ አይምሮ ባለቤቶችና ለለውጥ ከተዘጋጁ ሃይሎች የሚጠበቅ ነው፡፡

ስለሆነም የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱን ከፍተኛው ግብ ቀርቶ መሠረታዊ ግቡ እንኳ ይፈፀማል ብለው ለማስቀመጥና ለማመን የማይደፍሩት የአቋራጭ ስልጣን ፈላጊዎች ጉዳዩን የፕሮፖጋንዳ እና የአምልኮ ብለው ቢኮንኑት አይገርምም፡፡

ከላይ እንደተመለከተውና መሃመድ በተባሉት ፀሃፊ እንደተቀመጠው የሥርዓቱ ማብቂያ ሳይሆን ጥቂት ናቸውና የዜሮ ድምሩ ስብስቦች እርስ በርሳቸው የሚጫረሱበት ቀን ቅርብ በመሆኑ የመለስ ራዕይ አቀንቃኞችና ተከታዮች ጭንቀት ሊሆኑ አይችሉም፡፡

መለስ "ሁሌም ከቁጥቁጥ አሠራር እንውጣ፣ በትንንሽ ውጤቶች አንርካ፣ በስፋት እናቅድ፣ ታላላቅ ሥራዎች እንሥራ፣ ከዚህም ከዚያም አጠራቅመንና ከራባት ለብሠን እየለመንን ያገኘነውን ሃብት አግባብ ባለው ሁኔታ አብቃቅተን እንጠቀምበት፣ ህዝባችንን ሁሌም ተጠቃሚ እናድርገው፣ እናዳምጠው፣ ሲያርመን እንሠማው፣ ትክክሉን እንውሠድ፣ ሲሣሣት እናስተምረው፣"እንደሚልና ካልሠራንለትና ካልሠማነው "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አሊያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሃል" ምሳሌው እንደሆነ እናውቃለን፡፡

ለመለስ ከድህነት በላይ አዋራጅ ነገር እንደሌለ፣ በድህነት የተቆራመዱና ጠኔ እየገረፋቸው የሚኖሩ፣ የሚለብሡት አጥተው በእርዛት የሚቸገሩና መጠለያ አጥተው ባረንዳ ጎጆዎች ተጨፋፍቀው የሚያድሩ ዜጎች ሃገር ይዘን እንቅልፍ ተኝተን ልናድር አይገባም በሚለው ሃሣቡና ለዚህም ስኬት

በሚያደርገው እንቅልፍ የለሽ ትጋት ያረጋገጠ በመሆኑ ይህንኑ እንቅልፍ የለሽ ትጋት የሚጠይቅ ራዕይ ለማስቀጠል መታተርና ይህንኑ በተግባር አድርጎት ሌላውም እንዲያደርግ ላስተማረ መሪ ማዘንና ሙት ዓመቱን ከድህንት ጋር በሚደረግ የዘመቻ ሥራ ማሠብ ተገቢና ትክክል ነው እንጂ ፕሮፖጋንዳው ነው ቢባል ከስብስቡ የሚጠበቅና ከላይ በተዘረዘረው ፍሬ ሃሣብ መሰረት ከድህነትና ቁጠባ አንፃር የሚገለጹትን መሪ ድህነት ፈጣሪና ሙስና አስፋፊ በማለት የሚደረግ ማጠልሸት የባለራዕዩን መሪ ተከታዮች የሚያስገርም አይሆንም፡፡

የመለስ የአስተሳሰብና የድርጊት መርሆ ማዕከላዊ ነጥብ፦ ድሪቶ መጣፍ ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ማላበስ፣ ድህነትን መግታትና ድሃውን ከክፉ እልቂት መመከት ሳይሆን ድህነትን መርታትና በድህነት ለዘመናት ተጠምዶ የማቀቀውን ህዝብ የብልጽግና ምንጭ እንዲሆን ማብቃት ነው፤ ቀዳሚው ዓላማው የሚያስታግሠውን ሳይሆን፣ የሚፈውሠውን መሻት ነው፡፡ የደከመው የወደቀው፣ ለመትረፍ ከመፍጨርጨር አልፎ ኑሮውን አቸንፎ ምኞቱ ለወገኑና ለአገሩ መድረስ እንደሆነ ማሣደግ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ በላይ ራዕይና ባለራዕይነት ከወዴት ይገኛልና ነው ራዕዩን ለማስቀጠል የሚታትሩት ላይ ጠጠር እየተወረወረ ያለው? ጉዳዩ የዜሮ ድምርና የግልብነት በመሆኑ አይገርመንም፡፡

መለስ ሃሣብ ማፍለቅ፣ ከሌሎች የሚመጡ ሃሣቦችን በሃሣብ መሞገት፣ ለሌሎች ሃሣብ ክብር መስጠት ብቻ ሳሆን የያዙትን ሃሣብ ወደተግባር በማሻገርም በኩል የማዳገት ችሎታ እንዳለው አለም መስክሮለታል፡፡ የከሠሩትም ቢሆኑ ያውቁታል፣ ማወቃቸውንም ወደው ሳይሆን ሳይወዱና አምልጧቸው መበተደጋጋሚ መስክረዋል፡፡

የከሠሩት እንደሚሉት መለስ ሃሣብን በቀኖናነት አይመለከተውም፤ ሃሳቡን የሚፈልገው ለተግባር መመሪያነት ነው፡፡ አንድ ተግባር ሲታቀድ፣ ተግባሩ የሚመራበትን ሃሣብ ወደማፍለቅና መተንተን ይገባል፣ ያቀረበውን ሃሣብ መሠረት በማድረግም ፈጻሚ አካላት ሁሉ በብቃት እንዲሠማሩ ያስተምራል፣ የተግባሩን አፈፃፀም በቀጣይነት ያረጋግጣል፡፡ ይህንኑ ራዕይና ጥበብ አዲሶቹ አመራሮቻችን እና ተተኪዎቻቸው ቢያስቀጥሉና ለማስቀጠል ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለጽ መለሥን በሙት ዓመቱ አደራውን በሚወጣ ሥራ አስበው ቢውሉ ምኑ ነው የሚያስገርመው? እኛ ግን እንላለን ለሃሣብና ለምክንያት ቦታ የሌላቸውና ስለዜሮ ድምር ፖለቲካ የሚሠሩ ሃይሎች የሚሠጧቸው ትችቶች አያስጨንቁንም፣ አያስገርመንም፡፡

መለስ ገና ከጠዋቱ አገራችን ኢትዮጵያ ብዙሃን ብሔሮችና ሃይማኖቶችን ያቀፈች እንደመሆንዋ ልዩነታችንን አክብረን የተዘነጉ፣ የተናቁ ማንነታቸውንና እኩልነታቸው እውቅና አግኝቶ የአገሪቷ ዴሞክራሲያዊ አንድነትና ነፃና ህያው አካል እንደሆኑ በሠፊው መሥራቱ ፀሃይ የሞቀው ሃገር ያወቀው ሃቅ ነው፡፡ የሃገሪቱ አብይ ሃይል አርሦና አርብቶ አደሩ ነውና የኢትዮጵያ የዴሞክራሲም

ሆነ የልማት መሠረት ገጠሬው እንደሆነ በተግባር ማሣየቱም እንዲሁ ፀሃይ የሞቀው ሃገር ያወቀው ሃቅ ነው፡፡

ብዝሃነትን ማክበር የአገሪቱ ህልውና መሠረት መሆኑን አጽንኦት ሠጥቶ አስተምሯል፡፡ በገዛ አገራቸው ተዘንግተው የኖሩ፣ የተናቁና ማንነታቸውና እኩልነታቸው የተገፉ ወገኖች እኩልነታቸው ታውቆ በአገሪቱ ወሣኝ ተግባራት ተሣታፊና የውጤቱም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዚህም የሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊ አንድነትህያው አካል እንዲሆኑ በሠፊው ሠርቷል፤ ተጨባጭ ውጤትም አግኝቷል፡፡ የዚህ ተጨባጭ ውጤት ተጠቃሚ ከሆኑቱ እና የመለስን ራዕይ ማስቀጠል ስለኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት ከሚጨነቁቱ ሁሉ የሚጠበቅ መሆኑን የተገነዘቡ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሄረሠቦችና ህዝቦች በመለስ ሞት ቢያዝኑም፤ ሙት ዓመቱን ራዕዩን በሚያስቀጥሉ ሥራዎች አሥበው መዋላቸው የዜሮ ድምር ፖለቲካ መንገድ ሁሉ ዝግ መሆኑን ያመላከተች በመሆኗ ጥቂቶቹ "በመለሥ ራዕይ የተኮነንነው አንሶ አሁን ደግሞ በመለስ ራዕይ እንሠደድ" ቢሉን ግልብነት እንጂ ምክንያታዊነት ባለመሆኑ አይገርመንም፡፡

መለስ በአገራችን የህግ የበላይነት እንዲሠፍን የፍትህ አካላት፣ የህግ አስከባሪ ተቋማት እና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲጠናከሩ እና በዴሞክራሲ እሴቶች ላይ እንዲመሠረቱ ወሣኝ አመራር የሠጠ መሪ መሆኑም አውቀው በተኙት ካልሆነ በሥተቀር ልባቸውን ለከፈቱት ሁሉ ግልጽ ነው፡፡ ገና ከጠዋቱ የደርግ ባለሥልጣናት በህግና በህግ ብቻ እንዲዳኙ እና የበቀል እርምጃ እንዳይኖር ቁርጠኛ አቋም በመውሰድ ባለሥልጣናቱ በህግ ውሣኔ እንዲያገኙ በጽኑ ዕምነት አመራር የሠጠ መሆኑን የሚያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ የከሠሩት ሠዎች ከላይ በተመለከተው መሠረት እንደሚሉት መለስ የጠላውን የሚመታ እና ጋዜጠኞችና ተቃዋሚዎችን ለማሣደድ ሲል የፀረ ሽብር ህጉን አውጥቷል ብሎ አይከራከርም፡፡

የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በአገራችን እንዲጠናከር ገና ከመጀመሪያው በእምነት ሲታገል የኖረው መለሥ በተለይ የ1997 ዓ.ም ምርጫ በማንኛውም መለኪያ ነፃ፣ ግልጽና ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ በምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ የተመሠረተ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ የዴሞክራሣዊ ብርሃን የፈነጠቀ ተግባር እንዲከናወን ወደር የለሽ አመራር የሠጠ መሪ እንጂ ይህን እድል በመጠቀም ማሸነፍ እንደማይችሉ የሚገነዘቡትን በዓመጽና ግርግር ሥልጣን የሚሹ ሃይሎች እንደሚሉት ዓይነት ራዕይ ያለው መሪ እንዳልሆነ ሁላችንም እናውቃለንና ራዕዩን እናሥቀጥላለን፡፡ ሙት ዓመቱንም በሥራ አስበን እንውላለን፡፡

መለስ ለህግ የበላይነት የሚታገለውን ያህል ለይቅርታም ልብ የነበረው መሪ እንደነበር የሚገነዘቡት ሁሉ ራዕዩን በማስቀጠል ሥራ ቢጠመዱ ሊገርመን አይገባም፡፡ መለሥ የከሠሩት እንደሚሉን እና ከላይ በማሣያነት እንዳሠፈርኳቸው ነጥቦች ሳይሆን "ሠዎቹ ስህተታቸውን ካረሙና በህጋዊና

ሠላማዊ መንገድ እስከተንቀሳቀሡ በእያንዳንዷ ነገር መወዛገብና ሰዶ ማሣደድ ውስጥ መግባት አንፈልግም" የሚለውን ንግግሩን የምናስታውሠው ሠዎች መለስ በይቅርታ የሚያምን ሆደ ሠፊ መሪ እንደነበር እናምናለንና  መለስ "ጨካኝ ነው" የሚሉና "አምባገነን ነበር" የሚሉትን የከሡሩ ሠባኪዎች የሚሠማ ጆሮ የለንም፤ ዓይኖረንምም፡፡

የከሡሩት ፖለቲከኞችም ቢሆኑ መለስ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮች በአገራችን ህግ መሠረት ያቀረቡት የይቅርታ ጥያቄ በአግባቡ እንዲስተናገድ አስተዋይ አመራር የሠጠ መሪ መሆኑን በወቅቱ መስክረዋል፡፡ ከእሥር የተፈቱ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በህጋዊና ሠላማዊ መንገድ ተቃውሞአቸውን እንዲያራምዱ ነፃነት ያጎናፀፈ፣ ብሎም ከፓርቲዎቹ ጋር በጋራ የመሥራት ፈቃደኝነትን በተግባር ያረጋገጠ ዴሞክራሲያዊ አቋም እንዲወሠድ ብልህ የሆነ አመራር የሠጠ መሪ መሆኑንም ያውቁታል፡፡

ይህ አቋሙ ማንኛውም አይነት የፖለቲካ አቋም በነፃና ሠላማዊ መንገድ መራመድ አለበት ከሚለውና በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃውሞ ፖለቲካና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እውን እንዲሆን በድፍረት ካራመደው በሣል አቋም ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ተተኪ አመራሮቹም ይህንኑ ራዕይ ባያስቀጥሉና ለማስቀጠል ቃል ባይገቡ ነበር የሚገርመን እንጂ፤ ይህችን ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማትመቻቸውና ለሥልጣን የሚያበቃቸው ፖለቲካዊ ቁመና የሌላቸው ፓርቲዎችና የከሡሩ ሠዎች "የመለስ ራዕይ ገፋን፤ አደነቆረን" ቢሉን ከደንቆሮ የሚጠበቅ በመሆኑ አይገርመንም፡፡

መለስ ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ድንቅ ልጅ፣ የአፍሪካ አንደበት፣ ባለራዕ አፍሪካዊ መሪ… ወዘተ የሚሉ ስያሜዎችን ያተረፉለትን የተለያዩ ተግባራት ማከናወኑም ይታወቃል፡፡ የአፍሪካ ምርቶች ዋጋ እንዲሻሻል፣ ወደ አፍሪካ የሚፈሠው ኢንቨስትመንት፣ ብድርና እርዳታ እንዲጨምር፣ አፍሪካውያን በአየር ንብረት መዛባት ለሚደርሥባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲያገኙ እንዲሁም የዓለም የንግድ ስርዓት ለአፍሪካ እድገት የሚያመች እንዲሆን ለማድረግ በተገኙት መድረኮች ሁሉ ታግሏል፡፡ ትግሉንም ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጭምር በሠጡት ሽፋን አረጋግጠዋል፡፡

የአፍሪካውያን ጥቅም የሚረጋገጠው በተናጠል በሚደረግ መፍጨርጨር ሳይሆን በመሠረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም በመያዝ፣ በዓለም አቀፍ መድረኮች በአንድ ድምጽ በመሠለፍ መሆኑን መለሥ ከልቡ አምኖ ለዚህም ተግባራዊነት ከአፍሪካውያን መሪዎች ጋር በመመካከርና ጠቃሚ ሃሳቦችን በማቅረብ ተቀባይነትንና አክብሮትን ማትረፉን ህይወቱ ባለፈ ጊዜ የአፍሪካ መሪዎች በአንባቸው አረጋግጠው፤ ራዕዩን ለማስቀጠል ቃል በገቡ ጊዜ የከሡሩት ሁሉ "ጉዳዩ የፕሮቶኮል ነው" ብለው ማብጠልጠላቸውን አንዘነጋም፡፡ የሆነ ሆኖ ግን በርግጥም መለስ ባለራዕይ የአፍሪካ መሪ ነበርና ራዕዩን ለማስቀጠል ቃል የገቡት መሪዎች በሙት ዓመቱ ቀን  በኢትዮጵያ

ተገኝተው በተለይም በአረንጓዴ ልማት ሥራ አስበው በመዋል ቃል ኪዳናቸውን ማደሳቸው የሚጠበቅ ነበርና ባይገርመንም፤ በሌላ በኩል ግን የመሪዎቹን ጥልቅ ሃዘን "ፕሮፖጋንዳ ነው" ሲሉ ያብጠለጠሉ፡ ሃይሎች ጊዜው ደርሶ የመሪዎቹ መሪር ሃዘን ከልብና የመለሥን ታላቅነት የሚያረጋግጥ መሆኑን ሲረዱ ማፈራቸው አይቀሬ ነውና አሁንም የመታሠቢውን ሥነ-ሥርዓት "ፕሮፖጋንዳ ነው" ሲሉ ቢጮኹ ይህም የሚጠበቅና ከሥብስቦቹ የለመድነው በመሆኑ አይገርመንም፡፡

መለስ የላቀ ህዝባዊ ፍቅር ያለው መሪ ነበር፡፡ ይህ ህዝባዊ ፍቅር መለስ እያንዳንዱን ጉዳይ ከህዝቦች ጥቅም አኳያ እንዲመዝን ያደረገው መሆኑንም እንረዳለን፡፡ የህዝቦች ሠቆቃ የሚያንገፈግፈው፣ ለህዝቦች ጥቅምና ደህንነት ቀን ከሌት የሚጨነቅ፤ ይህንን ፍቅሩን የሁሉም የተግባራቱ አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎ የሚጠቀም መሆኑ መለሥን ባለራዕይ መሪ አድርጎታል፡፡ መለስ የህዝቦችን ፍላጎት የሚያነፈንፍ ለህዝብ ቅርብ ልብ ያለው መሪ መሆኑንም በተግባር አሣይቶ አልፏል፡፡ መለሥን የምናውቀው "ለእኔ አገር ማለት ህዝብ ማለት ነው፡፡ የአገር ፍቅርም ማለት ከህዝብ ፍቅር ውጪ ትርጉም የለውም" ሲል እንጂ እንደከሠሩቱ "ሃገር ማለት በህዝብ ሽፋን ስልጣን መያዝ ማለት ነው" ሲል አይደለም፡፡

ህዝብ በትክክለኛ ድርጅት ከተመራ ታሪክ ሊሠራ የሚችል መሆኑን አምኖ ወደ ጥቅሙ የሚያመራውን አቅጣጫ ለማሥያዝ መለስ ደክሞ መስመሩን አስይዞን አልፏል፡፡ ስለሆነም ይህን መስመር የመዘርጋትና የማስቀጠል ጉዳይ ድህነትን ከሚጠላ እና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ከሚሻ ትውልድ ሁሉ የሚጠበቅ ነውና አሁንም ራዕዩን እናስቀጥላለን፡፡

በመልካም ተግባራቸውና በሥብእናቸው ደምቀውና አንፀባርቀው ከመቃብር በላይ ስማቸው ጎልቶ ከሚሠማው ታላላቅ ሠዎችና አለማችን ለቅጽበት አይታቸው ካለፉ ተወርዋሪ ኮከቦች መለስ አንዱ ነው፡፡

ስለሆነም መለስ ለሁሉም ነበርና አሁንም የሁሉም ነው፡፡ ለአገራችን ህዝቦች ልማት ለእኩልነት፣ ለሠላም፣ ለዴሞክራሲ…. ባደረገው ተጋድሎ መለሥ የሁሉም ብሔረሰቦች አባል፣ የሁሉም ማህበረሠቦች የአርሦ አደሩ፣ የአርብቶ አደሩ፣ የወጣቱ፣ የሴቶች፣ የከተማ ነዋሪውና የባለሃብቱ አካል ሆኗልና ራዕዩን በሚያስቀጥሉ ሥራዎች ሲታሠብ ይኖራል፡፡

በመግቢያዬ አካባቢ እንደተመለከተው ይህ ታሪክ መለስን እንደ አበበ በመዝገብ ስሙ የሚያስታውስ ነው፡፡ አበበን እንደወልደገብርኤል ባየንበት ዓይን ደግሞ መለስን እንደ ገብረማርያም ክርስቲያን ነውና ይዘከር ዘንድ ሥርዓተ ቤተክርስቲያኑ ግድ ይለዋል፡፡

በህገ ቤተክርስትና እውቀቱ የሌላቸው እንኳ ቢሆኑ  አንድ ሠው ምድሪቷን ሊሰናበት ነፍስያው በአፀደ ገነት ትቆይ ዘንድ ከፀሎተ ፍትሃት ጀምሮ በሠልስቱ፤ በሠባቱ ፤ አርባ ሠማንያ፤ መንፈቅና ሙት ዓመቱ በፀሎትና በምጽዋት ይዘከራል፡፡ ተዝካርም ይወጣለታል፡፡

ስለሆነም መለስ እንደ ገብረ ማርያም ከግብአተ  መሬቱ ጀምሮ በህገ ቤተክርስትና በተቀመጠው አግባብ መሠረት "ግብኢ ነፍስየ ውስተ እረፍትኪ ለነፍሠ ገብሩ ገብረ ማርያም" ተብሎ መጽሃፈ ግንዘት ቢደገምለት፣ መዝሙረ ዳዊት ቢወረድለት፤ ሣዕታት ቢቆምለት ፤ በምጽዋትና ተዝካር ቢዘከር፤ የቤተክርስቲያኒቱ ግብር እንጂ የከሠሩት እንደሚሉት ቤተክርስቲያኒቱ ላይ የተደረገ ጫናና ጠለፋ አይደለም፡፡ የመለሥ የሚፈልገውን  እምነት የመከተልና ከዚሁም አገልግሎት የማግኘት የገብረማርያም መብት ነው፡፡

ስለሆነም ትቶት ያለፈው ገፁ ብዙ፣ አብነቱ አብሮን እንዳለ ጓድ መለስ በኢህአዴግ ሲታወስ ይኖራል፤ አቶ መለስ በመለስ ፋውንዴሽን ሲታሰብ ይኖራል፡፡ ገብረማርያምም ሠው በሥራው ይፀድቃል እንዲሉ በዚያ ቀን "ብራብ አላበላችሁኝምና፣ ብጠማ አላጠጣችሁንምና ብታረዝ አላለበሣችሁኝምና፣ ብታሠር አልጠየቃችሁኝምና እናንተ ርጉማን ከኔ ወግዱ" ከሚባሉት ሳይመደብ፤ ብንራብ አብልቶናልና፣ ብንጠማ የምንጠጣውን ሸቷልና፣ እንዳንታረዝም ደክሟልና ለታሠሩትም ይቅር ብሎ የእግዜሩን መገለጫ ይቅርታ አስተምሯልና፤ "እናንተ ብሩካን አለም ሳትፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግስተ ሠማያት ትወርሡ ዘንድ ወደእኔ ኑ" ከሚባሉት ወገን በቀኝ ይቆም ዘንድ በሙት ዓመቱ ቀን ይልቁንም የሠኔና ሠኞ ነገርም አጋጥሟልና የፆመ ፍልሠታዋን በረከት በሠማይም ሆኖ ሲቋደስ ይኖራል እንጂ ማንም በሡና ሥለሡ በተለየ አግባብ ፕሮፖጋንዳ ሲያደርገው አይኖርምም፤ የሚሻም ሃይል የለም፡፡ ማንም ስለመለስ ሥራውን ወርሦ መልካሙን ሁሉ እሱ በገባው  አግባብ ራዕዩን ያስቀጥላል እንጂ የሚያመልክ የለም፤ አይኖርምም፡፡ እኔም በየዓመቱ ባለብዙ ገጽታውን መለሥ በመተረክ መለስን አስባለሁ ገብረማርያምንም መንግስተሠማያትን ይወርስ ዘንድ ከፍካሬ ዘፃድቃን እስከ ----እወርዳለሁ፡፡ አሁን የተግባባን ይመስለኛል፡፡ቻዎ!